# ሊቅ ፣ ቅኔን ይዘርፋል

ተግባር በማይገልፀው ፣ በአርቲ ቡርቲ ወሬ ፣ ዜጋ ተዘናግቶ
ስም አይጠሬ አክራሪ ፣ ከየጉራንጉሩ ፣ ወጥቶ ተጠራርቶ
አሰሱም ገሰሱም ፣ እንደ አንበጣ መንጋ ፣ አራት ኪሎ ገብቶ
ዙፋኑን ባጠሩት ፣ ተምችና ኩብኩባ ፣ ጥላቻ ተዘርቶ
አገር እየናደ ፣ ሀብት እየዘረፈ ፣ አይጠረቃ በልቶ
እድሜ ቀጥል መስሎት ፣ ለስልጣን መቆያ ፣ አይነኬን ነክቶ
ትውልድን ያስፈጃል ፣ በቋንቋና ሀይማኖት ፣ አራጅ አዘጋጅቶ ።

መነሻው መቶ ዓመት ፣ የሚያነበንበው ፣ ሚኒሊክ ዳዊቱ
ዶግማና ቀኖናው ፣ አማራና ኦርቶድክስ ፣ ቀዳሚ ጠላቱ
ያናሳነት ስሜት ፣ በፈጠረው ቁስል ፣ እድገቱ ጥምቀቱ
በፈጠራ ታሪክ ፣ በጎጥ በመንደር ልጅ ፣ እየተኳተቱ
የሃሳብ ድኩማን ፣ በሰለጠነ ወግ ፣ ተሟግተው አይረቱ
እንምራህ የሚሉት ፣ የመንጋው እረኞች ፣ ያሉት ከበረቱ
ወንዝ የማያሻግር ፣ የአንበሳውን ደቦል ፣ ነካኩት በከንቱ
አስር ቢገላበጥ ፣ ስርአቱ የገማው ፣ ከቤተ መንግሥቱ ።

በአናሳነት ስሜት ፣ ውስጡ የታመመ ፣ ተንኳሎ ፣ ተንኳሎ
ከላይኛው እርከን ፣ እስከ ታች ሹማምንት ፣ ደነዝ ተኮልኩሎ
ቀድሞ የማናውቀው ፣ ባገር ያልነበረ ፣ አራሙቻ በቅሎ
እድሜ አለሙን ጥሬ ፣ ማገዶ የሚጨርስ ፣ የማይታይ በስሎ
አይን የሚጎለጉል ፣ በግፍ በጭካኔ ፣ ሴት አዛውንት ገድሎ
የዱር አራዊት ነው ፣ ባገር ላይ የመጣው ፣ በሰው ተመስሎ
ሰው እንዴት ይኖራል ፣ ቆሞ ከሚራመድ ፣ አራዊት ተዳብሎ ።

እቺ ዘለል ዘለል ፣ የጊዜ ጉዳይ ናት ፣ ሁሉም ይቀረፋል
ያክራሪ ዘረኞች ፣ ግፍና ጭካኔ ፣ ጨለማውም ያልፋል
አይዞህ የተባለው ፣ ጥጋብ ያናጠጠው ፣ ነገ አንገት ይደፋል
በጭካኔ ያረደ ፣ አይን የጎለጎለም ፣ ገድላቸው ይፃፋል
ለሁሉም ጊዜ አለው ፣ አስተዋይ አይቸኩል ፣ ሆድ ካገር ይሰፋል
ያልደከምክበትን ፣ አላምጥህ ሳትውጣት ፣ ሁሉንም ያስተፋል
የተኛን ቀሰቀስክ ፣ እንጃ መድረሻህን ፣ ሞት ላንተ ይከፋል
ቅንቅን ፣ ንብረት ሲዝረፍ ፣ ነገን እያሰበ ፣ ሊቅ ቅኔን ይዘርፋል ።

ታዛቢው

August 3, 2020